የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፳
አዲስ አበባ ጥር ፮ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No.20
ADDIS ABABA 14th January, 2015

## ማውጫ

አዋጅ ፰፻፸፪/፪ሺ፯ ዓ.ም

የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ (ማሻሻያ) አዋጅ ............................................................ገጽ ፯ሺ፱፻፵፬

## CONTENTS

Proclamation No. 872/2014

Copyright and Neighbouring Rights Protection (Amendment) Proclamation .......................Page 7944

### አዋጅ ቁጥር ፰፻፸፪/፪ሺ፯

### የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በየወቅቱ እያደገ የመጣውን የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ እንቅስቃሴ የሚመጥን የህግ ስርዓት ለመዘርጋት እና ባለመብቶች በተደራጀና በተጠናከረ አግባብ መብቶቻቸውን ማስተዳደር የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር እንዲቻል የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር ፬፻፲/፲፱፻፺፮ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፰፻፸፪/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### PROCLAMATION No. 872/2014

### A PROCLAMATION TO AMEND THE COPYRIGHT AND NEIGHBOURING RIGHTS PROTECTION PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the Copyright and Neighbouring Rights Protection Proclamation No. 410/2004 to provide legal protection that is compatible with an ever growing development of copyright and neighbouring rights and to create conditions enabling the right holders to administer their rights in an organized and enhanced manner;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Copyright and Neighbouring Rights Protection (Amendment) Proclamation No. 872/2014".

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 14.10

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. ማሻሻያ

የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር ፬፻፲/፲፱፻፺፮ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፴) ሥር የሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (በ) ተጨምሯል፡-

"(በ) የዕደ-ጥበብ ስራዎች፤"

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ ሥር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፴፩)፣ (፴፪)፣ (፴፫)፣ (፴፬) እና (፴፭) ተጨምረዋል፡-

"፴፩/ 'ሮያሊቲ' ማለት ከንግድ ስራ ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ ለሚውል በዚህ አዋጅ መሠረት ጥበቃ ለሚያገኝ ስራ በተጠቃሚው አማካኝነት ለባለመብቱ የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ ነው፤

፴፪/ 'የጋራ አስተዳደር ማህበር' ማለት የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ባለቤቶች መብቶቻቸውን በጋራ ለማስተዳደር የሚያቋቁሙት ማህበር ነው፤

፴፫/ 'የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር' ማለት ሮያሊቲ የሚከፈልበትን ስራ እና የተጠቃሚ ዎችን ማንነት መሠረት በማድረግ የሚሰበሰብን የሮያሊቲ መጠን ለማስላት ጥቅም ላይ የሚውል ዘዴ ነው፤

፴፬/ 'ባለቤት የሌለው ስራ' ማለት ባለቤት የሌለው ስለመሆኑ በፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠበት ስራ ነው፤

፴፭/ 'ለህዝብ ለመቅረብ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ስራዎች' ማለት ከሽያጭ ወይም ከኪራይ ውጪ በቀጥታ ለህዝብ በይፋ ለመከወን ወይም ለመታየት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ እና የእንካ ለእንካ ስምምነት ከሌለ በስተቀር

## 2. Amendment

The Copyright and Neighbouring Rights Protection Proclamation No. 410/2004 is hereby amended as follows:

1/ the following new paragraph (j) is added under sub-article (30) of Article 2 of the Proclamation:

"j) applied art;"

2/ the following new sub-article (31), (32), (33), (34) and (35) are added under Article 2 of the Proclamation:

"31/ 'royalty' means fees payable to an owner of a work protected under this Proclamation by the user of such work for commercial purpose;

32/ 'collective management society' means a society formed by the owners of copyright and neighbouring rights to jointly administer their rights;

33/ 'royalty scheme' means a method employed to calculate the amount of royalty collected from the users of work based on the type of work and the category of users;

34/ 'work without a master' means work which have been declared by the court of law as a work without a master;

35/ 'entry of works for public performance' means an entry of a foreign work, which is not administered by a collective management society established in Ethiopia except on the basis of reciprocity agreement for the purpose of public

በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋሙ የጋራ አስተዳደር ማህበራት የማይተዳደሩ ስራዎች ናቸው፡፡"

፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ የቀድሞው ንዑስ አንቀጽ (፫) ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

፬/ በአዋጁ ከአንቀጽ ፱ ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተጨምሯል፡-

"፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተቀመጠው ልዩ ሁኔታ መሰረት አንድ ቅጅ ለግል ጥቅም ፍጆታ ለማዋል ማባዛት የሚፈቀደው የሚያባዛው ግለሰብ በቅድሚያ የስራው ኦርጅናል ቅጅ ባለቤት ከሆነ ነው፡፡"

፭/ የአዋጁ አንቀጽ ፳ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፡-

"፩/ የኢኮኖሚ መብቶች የስራ አመንጪው በህይወት በሚቆይበት ዘመንና ከሞተ በኋላ ለወራሾቹ እስከ ፶ ዓመት ጸንተው የሚቆዩ ሲሆን የጥበቃ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው የስራ አመንጪው ከሞተበት ቀን ቀጥሎ ካለው እ.አ.አ. ጥር ፩ ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡"

፮/ በአዋጁ አንቀጽ ፳፰ ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተጨምሯል፡

"፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው በሪከርዲንግ ሌብሉ ወይም በመያዣው ላይ የተጻፈ ጽሁፍ የድምጽ ሪከርዲንግ ወይም ኦዲዮ-ቪዥዋል ስራ ፕሮዲውሰር መብት በተመለከተ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚቀርቡ ክርክሮች ላይ ፍሬ ነገርን የሚያስረዳ መነሻ ማስረጃ ይሆናል፡፡"

performance or display by any means other than sale or rent."

3/ Sub-article (2) of Article 6 of the Proclamation is deleted and the existing sub-article (3) is renumbered as sub-article (2).

4/ The following new sub-article (3) is added under Article 9 of the Proclamation:

"3/ Private reproduction of a published work in accordance with sub-article (1) of this Article shall be allowed if that physical person is the owner of an original copy."

5/ Sub-article (1) of Article 20 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

"1/ Economic rights shall belong to the author during his lifetime and to the heirs or legatees for fifty years after the death of the author, and the term of protection shall run from the 1st day of January following the death of the author."

6/ The following new sub-article (3) is added under Article 28 of the Proclamation:

"3/ A statement on the label of recording or on its container referred to in sub-article (1) of this Article shall be prima facie evidence of the facts stated thereon for the purposes of any proceedings brought under this Proclamation with respect to the rights of the producer of sound recording or audio visual work."

፯/ የአዋጁ አንቀጽ ፴ ተሰርዞ ነባሩ አንቀጽ ፴፩ እና ፴፪ እንደ ቅደም ተከተላቸው አንቀጽ ፴ እና ፴፩ ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

፰/ ከአዋጁ አንቀጽ ፴፩ (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) እንደተሸጋሸገው) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ክፍል ስድስት ተጨምሯል፡-

"ክፍል ስድስት
የጋራ አስተዳደር ማህበር

፴፪. የጋራ አስተዳደር ማህበር አመሰራረት

፩/ በዚህ አዋጅ ጥበቃ የሚያገኙ ስራዎች ባለመብቶች መብቶቻቸውን በጋራ ለማስተዳደር የሚያስችላቸውን የጋራ መብት አስተዳደር ማህበር ሊመሰርቱ ይችላሉ፡፡

፪/ የጋራ አስተዳደር ማህበር በጽሕፈት ቤቱ በሚሰጥ እውቅና የሚመሠረት ይሆናል፡፡

፫/ የጋራ አስተዳደር ማህበር የሚመሠረተው ትርፍ የማግኘት ላልሆነ ዓላማ ይሆናል፡፡

፬/ የጋራ አስተዳደር ማህበር አደረጃጀት በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

፴፫. የጋራ አስተዳደር ማህበርን ለመመስረት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

፩/ ለጽሕፈት ቤቱ የሚቀርብ የጋራ አስተዳደር ማህበር ምስረታ ዕውቅና ማመልከቻ ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተያይዞ በጽሁፍ መቅረብ ይኖርበታል፡-

ሀ) የአባላት የፈጠራ ስራ ዓይነት መግለጫ፤

ለ) የውስጥ አሰራር ደንብ፤

ሐ) የመመስረቻ ጽሁፍ፤ እና

መ) በስሩ የተቋቋሙ የዘርፍ ማህበራት እና የማህበራቱ አባላት ዝርዝር፡፡

7/ Article 30 of the Proclamation is deleted and the existing Article 31 and 32 are re-numbered as Article 30 and 31, respectively.

8/ The following new Part Six is added after Article 31 of the Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (7) of this Article):

"PART SIX
COLLECTIVE MANAGEMENT SOCIETY

32. Management Society

1/ Right holders of works protected under this Proclamation may form collective management society to jointly administer their rights.

2/ A collective management society shall be formed based on the recognition granted by the office.

3/ A collective management society shall be formed for non-profit purpose.

4/ The organization of a collective management society shall be determined by the memorandum of association.

33. Pre-conditions for the Formation of a Collective Management Society

1/ An application for recognition of the formation of a collective management society shall be submitted to the office in a written form accompanied with the following documents:

a) description of the types of members' creative works;

b) internal rules of regulations;

c) memorandum of association; and

d) list of sector associations established under it, and their respective individual members.

፪/ የጋራ አስተዳደር ማህበሩ በሥሩ የሚያቋቁማቸው የዘርፍ ማህበራት ቁጥር ከሶስት ማነስ የለበትም፡፡

**፴፬. <u>የጋራ አስተዳደር ማህበሩ ሥልጣንና ተግባራት</u>**

የጋራ አስተዳደር ማህበሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በዚህ አዋጅ ጥበቃ የሚደረግላቸውን እንዲሁም የውጭ አገር ጥበቃ ያላቸውን ሥራዎች ከሚጠቀሙ ሰዎች ሮያሊቲ የመሰብሰብ እና መብት ላላቸው አባላት የማከፋፈል፤

፪/ የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ ረቂቅ የሮያሊቲ ክፍያ ቀመር በማዘጋጀት ለጽሕፈት ቤቱ የማቅረብ፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ የማድረግ፤

፫/ የሮያሊቲ አሰባሰብንና አከፋፈልን አስመልክቶ ዝርዝር የአሰራር መመሪያ በማዘጋጀት ለጽሕፈት ቤቱ የማቅረብ፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ የማድረግ፤

፬/ ለአባላት ከሚከፈል የሮያሊቲ ክፍያ በህግ መሠረት ግብር ተቀናሽ በማድረግ አግባብ ላለው ገቢ ሰብሳቢ አካል ገቢ የማድረግ፤

፭/ ለህዝብ ለመቅረብ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ስራዎችን ለማቅረብ ከሌሎች አገራት ለሚገቡ የባንድ ወይም የክወና ቡድኖች እንዲሁም ለስነ ጥበብ ስራዎች ዓውደ ርዕይ አቅራቢዎች በተመጣጣኝ ክፍያ ፈቃድ የመስጠት፤

፮/ ባለቤት የሌላቸው ስራዎችን ሮያሊቲ በመሰብሰብ ለጽሕፈት ቤቱ ገቢ የማድረግ፤

፯/ የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በራሱ ስም የመክሰስና የመከሰስ፤

2/ The number of sector associations established under a collective management society may not be less than three.

**34. <u>Powers and Duties of the Collective Management Society</u>**

A collective management society shall have the following powers and duties to:

1/ collect royalties from users of works protected under this Proclamation as well as works protected abroad and distribute same to the right holders;

2/ by taking into account the country's objective reality, prepare and submit to the Office royalty scheme and implement same upon approval;

3/ prepare and submit to the Office working manual for collection and distribution of royalty and implement same upon approval;

4/ withhold income tax in accordance with law from royalties distributed to members and pay same to the appropriate revenue collecting body;

5/ grant permit, upon payment of reasonable fee, to foreign musical bands or performing groups for entry of works for public performance or as well as foreign exhibitors of fine arts;

6/ collect royalties from works without masters and pay same to the Office;

7/ own property, enter into contract, sue and be sued in its own name;

፰/ በማንኛውም ጊዜ በጽሕፈት ቤቱ ሲጠየቅ የሥራ ሪፖርት የማቅረብ፣

፱/ ለተመሠረተበት ዓላማ አስፈላጊ የሆኑ በጽሕፈት ቤቱ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት የማከናወን፡፡

**፴፭. በጀት**

፩/ የጋራ አስተዳደር ማህበር በጀት ከሚከተሉት ምንጮች በሚገኝ ገቢ የሚሸፈን ይሆናል፣

ሀ) በዚህ አዋጅ መሰረት ከሚሰበሰብ የሮያሊቲ ክፍያ ከሚደረግ ተቀናሽ፣

ለ) ከአባልነት መዋጮ፣

ሐ) ከሌሎች ተያያዥ አገልግሎቶች የሚሰበሰብ የአገልግሎት ክፍያ።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) መሠረት የሚደረገው ዓመታዊ ተቀናሽ መጠን ከሚሰበሰበው አጠቃላይ ሮያሊቲ ከሰላሳ በመቶ መብለጥ የለበትም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው የሮያሊቲ ተቀናሽ መጠን ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት በየዓመቱ ለጽህፈት ቤቱ ቀርቦ መፅደቅ አለበት፡፡

**፴፮. የሂሳብ መዛግብት**

፩/ የጋራ አስተዳደር ማህበሩ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትን መያዝ አለበት፡፡

፪/ የጋራ አስተዳደር ማህበሩ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በውጪ ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

፫/ የጋራ አስተዳደር ማህበር ኦዲት የተደረገውን ያለፈውን ዓመት የሂሳብ ሪፖርት እና የቀጣዩን ዓመት በጀት ለጽሕፈት ቤቱ ያቀርባል፡፡



8/ submit performance report at any time when requested by the Office;

9/ perform other functions necessary for the achievement of its objectives as may be assigned to it by the Office.

**35. Budget**

1/The budget of a collective management society shall be drawn from the following sources:

a) deductions made from the royalties collected in accordance with this Proclamation;

b) membership contributions;

c) fees collected from other related services.

2/ The annual deduction to be made pursuant to sub-article (1) (a) of this Article may not exceed thirty per cent of the total collected amount of royalty.

3/ The amount of deduction to be made in accordance with sub-article (2) of this Article shall be submitted annually to the Office for approval before its implementation.

**36. Books of Accounts**

1/ A collective management society shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of a collective management society shall be audited annually by external auditors.

3/ A collective management society shall submit audited financial reports of the preceding year and its budget of the following year to the Office.

፬/ የጋራ አስተዳደር ማህበር የበጀት ዓመት በኢትዮጵያ በጀት ዓመት መሰረት ይሆናል፡፡

፭/ ጽሕፈት ቤቱ በማናቸውም ጊዜ የጋራ አስተዳደር ማህበሩ የፋይናንስ ሪፖርት እንዲያቀርብ ሊጠይቅ እንዲሁም የሒሳብ መዛግብቱን ሊመረምር ይችላል፡፡

፴፯. <u>እውቅናን ስለመሰረዝ</u>

ጽሕፈት ቤቱ በሚከተሉት ምክንያቶች የማንኛውንም የጋራ አስተዳደር ማህበር እውቅናን ሊሰርዝ ይችላል፡-

፩/ በዚህ አዋጅ ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች ተጻራሪ የሆኑ ተግባራትን ፈጽሞ ሲገኝ፤

፪/ በአባላት አብላጫ ድምጽ የጋራ አስተዳደር ማህበሩ እንዲፈርስ የተወሰነ ሲሆን፤ ወይም

፫/ ሥልጣን ባለው የዳኝነት አካል የጋራ አስተዳደር ማህበሩ እውቅና እንዲሰረዝ ውሳኔ የተላለፈበት ሲሆን ነው።

፴፰. <u>ሮያሊቲ የመክፈል ግዴታ</u>

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት ጥበቃ የሚያገኝ ማንኛውንም ስራ ለንግድ ዓላማ ጥቅም ላይ የሚያውል ማንኛውም ሰው የሮያሊቲ ክፍያን ለሚመለከተው የጋራ አስተዳደር ማህበር የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡

፪/ የሮያሊቲ ክፍያ የሚፈጸምባቸው ስራዎች ምድብ እና ክፍያ ሊፈጽሙ የሚገባቸው ተጠቃሚዎች ዝርዝር የጋራ አስተዳደር ማህበራት በሚያቀርቡት የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተመሥርቶ በጽሕፈት ቤቱ የሚወሰን ይሆናል፡፡

4/ The budget year of collective management society shall be the Ethiopian budget year.

5/ The Office may, at any time, request a collective management society to submit a financial report and inspect its books of accounts.

37. **<u>Revocation of Recognition</u>**

The Office may revoke recognition granted to any collective management society on the following grounds:

1/ when it carries out acts contrary to its powers and duties stipulated in this Proclamation;

2/ when members decide by majority vote to dissolve the collective management society; or

3/ when a court of law having jurisdiction orders the revocation of recognition of the collective management society.

38. **<u>Obligation to Pay Royalty</u>**

1/ Any person who uses any works protected under this Proclamation for commercial purpose shall have the obligation to pay royalty to the relevant collective management society.

2/ Category of works for which royalty payment is to be made and list of users subject to pay royalty shall be decided by the Office based on proposals submitted by the collective management societies.

**፴፱. ባለቤት ከሌላቸው ሥራዎች ስለሚሰበሰብ ሮያሊቲ**

፩/ ጽሕፈት ቤቱ የሥራውን ዓይነት ግምት ውስጥ በማስገባት ባለቤት ከሌላቸው ሥራዎች የሚሰበሰብ የሮያሊቲ ክፍያን ሊሰበስብ የሚገባውን የጋራ አስተዳደር ማህበር በመለየት ያሳውቃል፡፡

፪/ ባለቤት ከሌለው ስራ የሚሰበሰብ የሮያሊቲ ክፍያ መጠን በተመሳሳይ ወቅት ለተመሳሳይ ሥራ በጋራ አስተዳደር ማህበሩ ከሚሰበሰብ የሮያሊቲ መጠን ጋር እኩል ይሆናል፡፡

፫/ ባለቤት ከሌላቸው ሥራዎች የሚሰበሰብ ሮያሊቲ በጽሕፈት ቤቱ አማካኝነት በቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ልማት ዘርፍ ለሚከናወኑ ተግባራት ድጋፍ የሚውል ይሆናል፡፡"

፱/ የአዋጁ ነባሩ ክፍል ስድስት ክፍል ሰባት ሆኖ በዚሁ ክፍል ከአንቀጽ ፴፫ እስከ ፴፮ ያሉት ነባር ድንጋጌዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፵ እስከ ፵፫ ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

፲/ የአዋጁ አንቀጽ ፵፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) እንደተሸጋሸገው) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፦

"፩/ የኢትዮጵያ የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን የቅጅ ወይም ተዛማጅ መብት ባለቤት በሚያቀርበው ማመልከቻ መሰረት አመልካቹ መብቱን የጣሱ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን ዕቃዎች ወይም በራሱ አነሳሽነት የመብት ጥሰት ያስከትላሉ ብሎ ያመነባቸውን ዕቃዎች በቁጥጥሩ ሥር መያዝ ይኖርበታል፡፡"

**39. Royalty Collected from Works Without Masters**

1/ The Office shall, by taking into account the types of works, identify and notify the collective management society which shall be responsible to collect royalty from works without masters.

2/ The amount of royalty to be collected from a work without a master shall be equal to the amount of royalty collected from other similar work by the collective management society within a specific period of time.

3/ Royalties collected from works without masters shall be used by the office to support activities carried out for the promotion of protection of copyright and neighbouring rights."

9/ The existing Part Six of the Proclamation is renumbered as Part Seven and the existing Articles 33 to 36 of this part are re-numbered as Articles 40 to 43, respectively.

10/ Sub-article (1) of Article 42 of the Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article) is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

"1/ The Ethiopian Customs and Revenue Authority shall, based on a written application of the owner of copyright or neighbouring right, retain under its control goods, which in the opinion of the applicant infringe his right or, based on its own initiative, it believes that they may cause infringement of rights."

፲፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፵፫ (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) እንደተሸጋሸገው) ሥር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፬) እና (፭) ተጨምረዋል፡-

"፬ ጥበቃ ያገኙ መብቶችን ሆነ ብሎ የጣሰ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተደነገገው የእስራት ቅጣት በተጨማሪ ከብር ፳፭ሺ በማያንስ እና ከብር ፶ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፭/ ጥበቃ ያገኙ መብቶችን በከፍተኛ ቸልተኝነት የጣሰ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) ከተደነገገው የእስራት ቅጣት በተጨማሪ ከብር ፭ሺ በማያንስ እና ከብር ፳፭ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡"

፲፪/ የአዋጁ ነባሩ ክፍል ሰባት ክፍል ስምንት ሆኖ በዚሁ ክፍል ከአንቀጽ ፴፯ እስከ አንቀጽ ፵ ያሉት ነባር ድንጋጌዎች እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፵፯ እስከ አንቀጽ ፶ ሆነው ተሸጋሽገው የሚከተሉት አዲስ አንቀፅ ፵፬፣ ፵፭ እና ፵፮ ተጨምረዋል፡-

"፵፬. <u>የዳኝነት ሥልጣን</u>

፩/ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ከውል ውጭ ስለሚደርስ ሃላፊነትን የሚመለከቱ ጉዳዮች በስተቀር የፍትሐ ብሔር ክርክሮችን የመዳኘት ስልጣን የሚኖረው ጽሕፈት ቤቱ የሚያቋቁመው የአእምሯዊ ንብረት ትሪቡናል ይሆናል፡፡

፪/ የአእምሯዊ ንብረት ትሪቡናሉ ውሳኔ የህግ ስህተት ተፈጽሞ ተዛብቷል በሚል ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በተሰጠ በ፷ ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

11/ The following new sub-article (4) and (5) are added under Article 43 of the Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article):

"4/ Whosoever intentionally violates a right protected under this Proclamation, shall in addition to the imprisonment stipulated under sub-article (1) of this Article, be punished with a fine not less than Birr 25,000 and not exceeding Birr 50,000.

5/ Whosoever by gross negligence violates a right protected under this Proclamation, shall in addition to the imprisonment stipulated under sub-article (2) of this Article, be punished with a fine not less than Birr 5,000 and not exceeding Birr 25,000."

12/ The existing Part Seven of the Proclamation is re-numbered as Part Eight and the existing Articles 37 to 40 of this part are re-numbered as Articles 47 to 50, respectively, and the following new Article 44, 45 and 46 are added:

"44. **<u>Power of Adjudication</u>**

1/ Except cases related to extra-contractual liability, the power of adjudication of civil cases arising in relation to this Proclamation, shall be vested in the Intellectual Property Tribunal to be established under the Office.

2/ An appeal against the decision of the Intellectual Property Tribunal may be taken to the Federal High Court by an aggrieved party on question of law within 60 days from the date of the decision.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የአእምሯዊ ንብረት ትሪቡናል እስኪቋቋም ድረስ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘ የሚነሱ የፍትሐብሔር ክርክሮች በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚታዩ ይሆናል፡፡

**፵፭. <u>በህግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል ላይ ስለሚፈጸም ቅጣት</u>**

በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በወንጀል ህግ አንቀጽ ፴፬ በተመለከተው መሠረት በዚህ አዋጅ ጥበቃ ባገኙት ቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥሰት ወንጀል ተካፋይ በሚሆንበት ጊዜ በወንጀል ሁ አንቀጽ ፺ መሠረት ይቀጣል፡፡

**፵፮. <u>ውሳኔዎችን ለሕዝብ ስለማሳወቅ</u>**

ጽሕፈት ቤቱ በቅጅና ተዛማጅ መብት ጥሰት የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ማንኛውንም ጉዳይ ሰፊ ሥርጭት ባለው የብዙሃን መገናኛ ዘዴ እንዲሰራጭ ያደርጋል፡፡"

**፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር ፮ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

3/ The regular courts shall continue to adjudicate civil cases arising in relation to this Proclamation until the establishment of the Intellectual Property Tribunal pursuant to sub-article (1) of this Article.

**45. <u>Punishment Applicable to Legal Person</u>**

According to Article 34 of the Criminal Code, when a legal person participate in infringement of copyright and neighbouring rights criminal offence protected under this Proclamation, be punished in accordance with Article 90 of the Criminal Code.

**46. <u>Publicizing Decisions</u>**

The Office shall publicize final decisions on any copyright and neighbouring rights infringement through mass-media having wide coverage".

**3. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 14th day of January, 2015.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**